# Union of Tigreans in North America (UTNA)

ማሕበር ተጋሩ ሰሜን ኣሜሪካ (ማተሰኣ)

P.O.BOX 73736
Washington, DC 20056

Tel. (202) 265-8702
Fax. (202) 265-8703


---

## በአፋር ክልል የተፈፀመውን የሽብር ተግባር አስመልክቶ
## ከትግራይ ተወላጆች ማኅበር በሰሜን አሜሪካ የተሰጠ መግልጫ

የኤርትራ መንግሥት ኢትዮጵያ ሃገራችን ድህነትን ታሪክ ለማድረግ እያደረገች ያለውን ፈታኝ ትግል ለማደናቀፍ በተለያዩ አቅጣጫዎች የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የማተራመስ ተግባሩን ከተያያዘው ውሎ አድሯል፡፡

ይህንን እኩይ ተግባሩን እንዳሰበው ባይሆንም በተለይ በትግራይ እና በኣፋር ክልል የህዝቡን ሰላምና መረጋጋት በማወክ የትግራይ እና የኣፋር የኢንቨስትመንት ፍሰትና የቱሪዝም ኢንዱስትሪ እድገት ላይ ተፅእኖ እየፈጠረ ለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡

ሻዕብያ በተለያዩ ወቅቶች በዓዲ ዳዕሮና ሑመራ የህዝብ መጓጓዣዎችና ተቋማት ላይ ቦምብ በማጥመድ የህይወትና ንብረት ውድመት እንዳደረሰ ይታወቃል፡፡ በተለይ ደግሞ በጥር 7/2004 ዓ/ም የአገራችን ታሪካዊና የቱሪስት መስህብ የሆነውን የኣፋር ክልል በልዩ ስሙ አርታዕሌ የተባለውን ኣካባቢ በመጎብኘት ላይ የነበሩ ቱሪስቶችና ኢትዮጵያዊያን ላይ የግድያና የጠለፋ ተግባር መፈፀሙን የሰማነው በድንጋጤና በከፍተኛ ሃዘን ነው፡፡

የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት የሻዕብያ መንግሥት የአሸባሪነት ተግባርን ለማስቆም ማዕቀብ እንዲጣልበት የወሰነ ቢሆንም እስከ ዛሬ ድረስ ግን የአሸባሪውን መንግሥት እኩይ ተግባር ለማስቆም የሚያስችል ይህ ነው የሚባል ተግባራዊ ለውጥ ኣላመጣም፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ባወጣው መግለጫም የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታ ምክር ቤት በሻዕቢያ መንግሥት ላይ ተገቢውን እርምጃ የማይወስድ ከሆነ ኢትዮጵያ ራሷን የመከላከልና ሉዓላዊነቷን የማስከበር መብቷን በመጠቀም አስፈላጊውን እርምጃ እንደምትወስድ ገልጿል፡፡

እኛ የትግራይ ተወላጆች ማኅበር በሰሜን አሜሪካ አባላትና ደጋፊዎች ይህንን በሻዕቢያ የተፈፀመውን የሽበራ ተግባር በጥብቅ እያወገዝን ሻዕብያ በኢትዮጵያ በተለይ ደግሞ የኤርትራ ኣጎራባች በሆኑ የትግራይና የኣፋር ድንበር አካባቢዎች የሚኖረው ህዝባችን የዕለት ተዕለት የስጋት ኑሮ አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱና በአካባቢው በልማት፣ በኢንቨስትመንትና በቱሪዝም ፍሰት ላይ ተጽእኖ እያሳረፈ በመሆኑ መንግሥታችን የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የማስከበር መብቱን በመጠቀም ይህንን የአፍሪካ ቀንድ የሰላም ስጋት የሆነውን ኃይል ሽበራዊ ተግባርና ጥቃት ለማቆምና የህዝብን ደህንነት ለመጠበቅ ዘላቂ መፍትሄ እንዲያረጋግጥ በትግራይ ተወላጆች ማኅበር በሰሜን አሜሪካ አባላትና ደጋፊዎች ስም እየጠየቅን መንግሥት ይህንን ዘላቂ ሰላም ለማምጣት በሚያደርገው ማንኛውም እንቅስቃሴ በሙሉ አቅማችን የምንደግፍ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

የትግራይ ተወላጆች ማኅበር በሰሜን አሜሪካ

ዋሽንግተን ዲሲ - ጥር 18/2004 ዓ/ም